ከሲመሽ ተገኝ

# <u>የፖለቲካ ውርዴዎች</u>

ነፍሱን ይማረውና፣ አሌክሳንደር ፍሌሚንግ የተባለው የስኮትላንድ የሕክምና ጠበብ፣ ፔኒሲሊን የተባለውን ሁለገብ አንቲባዮቲክ ፈልስፎ፣ ቂጢኝ የሚባለው፣ በግብረስጋ ግንኙነት ይተላለፍ የነበረው በሽታ፣ በቀላሉ መፈወስ ከመጀመሩ በፊት፣ እንደ ቂጢኝ የሚፈራ በሽታ አልነበረም። ብዙ የባህል መድሃኒቶች ተሞክረውበት ግማሾቹ በሽታውን ለጊዜው እንዲከስምና እንዲደበቅ ሲያደርጉ፣ እንደ ክብረ ሰማይ ዓይነቱ፣ በበሽተኛው ቁስል ላይ በዱቄት መልክ ተቀምመው የሚነሰነሱ መድሃኒቶች ደግሞ፣ በሽተኛውን በጣም የሚያሰቃዩ ነበሩ። በተለይም የቂጥኝ በሽታ ተፈወሰ ከተባለም በኋላ የነበረበት ከፍተኛ ችግር፣ የዳኑት ሰዎች ቀደም ሲል ከነበረባቸው በሽታ ጋር የተያያዙ ብዙ ውስብስብ ችግሮች ስለሚኖሩባቸው ጤናቸው የተሟላ አልነበረም። እነዚህ ቂጢኝ ይዟቸው ዳኑ የሚባሉ ሰዎች <u>“ውርዴ”</u> ተብለው ይታወቁ ነበር። ሰውነታቸው በህመሙ በጣም ስለሚጎዳ፣ በቀላሉ ለብዙ በሽታዎች የተጋለጡና፣ አንዳንድ የምግብ ዓይነቶችም በሽታቸውን ስለሚቀሰቅሱባቸው ከብዙ የምግብ ዓይነቶች ሁሉ የተከለከሉ ነበሩ። በእንግሊዞቹ ብሂል ‘Birds of same feather flock together’ እንደሚባለው ሁሉ፣ በአማርኛ አነጋገርም ተመሳሳይ ተረት በቂጢኞሞች ላይ ይተረታል። ይኼውም *“የቂጢኞም ውሎ ከውርዴ ነው”* የሚል ነው። የተነሳሁት የቂጢኝን በሽታ ታሪክ ለማቅረብ ወይም ስለመድሃኒቱ መገኘት የምሥራች ለማብሰር ሳይሆን፣ ፖለቲካ ውስጥ ገብተው ከተተፉ በኋላ፣ እንደ እባብ ቆዳቸውን እየገለፈፉና እየለዋወጡ፣ እንደ አዲስ ፖለቲከኛ ብቅ እያሉ፣ በሃገራችን የፖለቲካ መድረክ ውስጥ ገብተው የሚቧችሩትንና የሚዘባርቁትን ሰዎች ሳይ፣ አባባሉ በደንብ የሚገልጻቸው ስለመሰለኝ ነው እንደ ርዕስ አድርጌ የወሰድኩት።

መቼም ማንም ሰው፣ እንደፖለቲከኞቹ ዓይኑን በጨው አጥቦና ደፍሮ ብዕሩን አሹሎ በየጋዜጣው፣ በየመጽሄቱና በየድረ ገጹ ላይ ባይጽፍና ባይከራከርም፣ ፖለቲከኛ ሆነም አልሆነም፣ የሃገሩ ነገር ሲነሳ መቆርቆሩ ስለማይቀር፣ ስለሃገሩ ጉዳይ መናገሩም ሆነ መከራከሩ አይቀሬ ነው። ታዲያ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚያስገርመው፣ አንዳንዶቹ የሃገር ጉዳይ ለነሱ ብቻ መተው ያለበትና፣ የሃገሪቱ ፖለቲካ እነሱን ካጣ ዕለቱን ዓይኑ ጠፍቶ ሃገሪቱ በጭፍን የምትሄድ ይመስላቸዋል መሰለኝ፣ ከፖለቲካ መድረክ አንወርድም ብለው ሙጭጭ ብለው ሲንገታገቱ መታየታቸው ነው። ታዲያ ፖለቲካ ውስጥ መቆየት ምን ነውር አለበት አትበሉኝ፣ እኔ የምለው አንድ ዓላማ ኖሯቸው በዚያ ጸንተው፣ ያንን ከግብ ለማድረስ ሲሉ ዕድሉን እስኪያገኙ ድረስ ሲታገሉና ከፖለቲካ መድረክ ሳይወርዱ የኖሩትንና እየታገሉ ያሉትን አይደለም።

ላወሳ የፈለግሁት እነዚህን፣ በጠመንጃ አፈሙዝ ተደግፈውም ሆነ ወይም አጭበርብረው፣ በአንድ የታሪክ አጋጣሚ፣ አንዴ ፖለቲካ መድረክ ላይ ወጥተው የነበሩትንና፣ በዚያ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ስንት ጥፋትና፣ ውድመት

በሃገርና በሕዝብ ላይ ካደረሱ በኋላ፤ ከመድረክ ገለል ብለው ላደረጉት ጥፋት ተጸጽተው መደበቅና ማፈር ሲገባቸው፤ ያ ሥልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን የለመዱት ክብር፤ ማስፈራራት፤ የህዝብ ንብረትና መብት መግፈፍና በሰው ሕይወት ላይ ፈላጭ ቆራጭ መሆን ውል ውል እያላቸው፤ ተመልሰው ወደ ሥልጣን ለመውጣት የሚፍጨረጨሩትንና የሚቅበዘበዙትን *"የፖለቲካ ሰዎች ነን"* ባዮች ነው።

የሩቁን ዘመን ትተን፤ ከ1966 ዓም ወዲህ እንኳን፤ በደርግና በወያኔ የአገዛዝ ዘመን ወደ ስልጣን ኮርቻ ከተፈናጠጡ በኋላ የተተፉ ሰዎች፤ ለስንት ጥፋት ተጠያቂ መሆናቸውን ረስተው፤ እነሱ ቢረሱ የተበደለው ሕዝብ ይረሳ ይመስል፤ ተመልሰው ወደ መድረክ ለመምጣት ሲሽሎኮሎኩ ሳይ ስለነሱ አፍራለሁ። እነሱማ ምን ሐሊና አላቸውና ያፍራሉ? እነሱን ወክለን እኛው እንፈርላቸው እንጂ። እነዚህ ሰዎች ሐሊና ቢኖራቸው ኖሮ፤ በቅርቡ ተይዞ ሄግ የሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት የጦር ወንጀለኞች ፍርድ ቤት እንደቀረበው እንደ ራዶቫን ካራድዚች ጺማቸውን አጎፍረው፤ ጸጉራቸውን አንዠርግገው ሌላ ሰው መስለው ተደብቀው መኖር እንጂ፤ አንዴ ፖለቲከኛ ነኝ አንዴ ኢትዮጵያን የማድን እኔ ነኝ እያሉ ሰው ፊት መቅረብ የነበረባቸው አልነበሩም።

የቀይ ሽብር ወንጀለኞች፤ የወያኔ ሹሞች ሁሉ ሳይቀሩ ኢትዮጵያን ለማዳን መጥተናል፤ ብለው ሊሰብኩን ይፈልጋሉ። በተለይ በደርግ ዘመን የነበሩትን ወንጀለኞች፤ ዘመኑ ትንሽ እየረዘመ በመሄዱ አንዳንዶቹን መርሳትና መዘንጋት ሳንጀምር የቀረን አይመስለኝም። የሚያስገርሙኝ ግን እነዚህ ፈጣጣዎቹና ዓይን አውጣዎቹ፤ ትናንትናና ከትናንት ወዲያ ከወያኔ ጋር እጅና ጓንት የነበሩና አብረው ሥልጣን ላይ ቁጭ ብለው ሃገር ሲያስገነጥሉ፤ የሃገሪቱን መከላከያ ሠራዊት ሲበትኑ፤ በከተማ ውስጥ በሰላማዊ ሠልፉም በጋዜጣውም ሲቃወማቸው የነበረውን ኃይል ከሥራ በመቀነስ ሽፉን ሲያባርሩ፤ ሃገሪቱን በጎሳ ከፋፍለው ሲያናክሱ የኖሩት ሁሉ፤ ገና ያፈሰሱት ደም ከእጃቸው ላይ ሳይደርቅና ሰለባዎቻቸው እንኳን ከቁስላቸው ሳያገግሙ፤ ተቃዋሚ ነን ብለው ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ ነው።

ባለፈው በደርግ ዘመንና አሁንም በዘመነ ወያኔ እንደምናየው እንደነዚህ ሰዎች አመለካከት፤ ማንኛውም ሥርዓት፤ እነሱ ውስጡ እስካሉበትና አብረው የሃገሪቱን ፖለቲካ እስካመሱበትና እስካቦኩበት ጊዜ ድረስ፤ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክል ነበር፤ ግን በጥቅምም ሆነ በሥልጣን ተጣልተው ሲያባርራቸው፤ የዚያን ጊዜ ነው ደርግም ፋሺስት፤ ወያኔም ዘረኛ፤ ሃገር አጥፊና ጸረ ኢትዮጵያ የሚሆነው። እስከዚያው ድረስማ የሥርዓቱ አቀንቋኞችና አውዳሾች ሆነው፤ (More Catholic than the pope) እንደሚባለው ከዋናው ደርግና ወያኔ ይበልጥ ደርግና ወያኔ ሆነው፤ በሕዝብና በሃገር ሲያላግጡ የነበሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች እኮ ዕድል አግኝተው ሥልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጠው በነበሩበት ጊዜ፤ በተደጋጋሚ በቴሌቪዥንም ሆነ በራዲዮ እየቀረቡ፤ ስንት ሃገሪቱን የሚጎዳና ሕዝብን የሚያናክስ የእብሪትና የድንቁርና መርዝ ሲረጩ የነበሩና የገለማ አስተዳደር በሕዝብ ጫንቃ ላይ ጥለው ስንት ሕዝብ ያስለቀሱና የፖለቲካ ህመማቸው ገና በደንብ ያልለቀቃቸው *"የፖለቲካ ውርደዎች"* ናቸው።

ለምሳሌ ያህል፣ የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ የነበረውን፣ ገብሩ አስራትን ሁልጊዜ የማስታውሰው በአንድ አባባሉ ነው። ይኸውም የግል ጋዜጦች መታተም ጀምረው በየቦታው ሲሰራጩ፣ ትግራይ ክልል ውስጥ ብቻ ለምን እንደማይገቡ ሲጠየቅ *“እኔ ክልል ውስጥ ቆሻሻ ወረቀቶች እንዲገቡ አልፈቅድም፤”* አለ ተብሎ፣ ጉድ ያለው ንግግር እንዳደረገ ተወስዶ፣ በመሰሎቹ እንደ ትልቅ ጀግና ተቆጥሮ፣ ሲሞካሽ ነበር። እንዲያውም በክልሉ መግቢያ ኬላዎች ላይ፣ ፈታሽ አቁሞ፣ የግል ጋዜጣዎች እንደኮንትሮባንድ ዕቃዎች እየተፈተሹ ይወረሱ ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ፣ በወያኔ ምክር ቤት ቁጭ ብሎ የኢትዮጵያን አካል አጨብጭቦ ያስገነጠለና የትግራይን ሕዝብ አደንቁሮ ለመግዛት ሲል፣ እሱና ካድሬዎቹ ከሚግቱት ርካሽ ፕሮፓጋንዳ በስተቀር፣ ሌላ ለየት ያለ አመለካከት ያለው ጋዜጣ የማንበብ መብቱን ሳይቀር ገፍፎ የነበረ ጸረ ዲሞክራሲ ግለሰብ፣ አሁን ከወያኔ ተጣልቻለሁ ብሎ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ እየተዘዋወረ ስለወያኔ መጥፎነትና ስለእሱ ተቃዋሚነት ሊያስረዳና ከወያኔ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ነጻ ሊያወጣን እንደተዘጋጀ ሊያሳምነን ሲሞክር፣ ሰውየውስ ያ ሁሉ ሥልጣንና ኃይል ከእጁ ተፈትልኮ ስለወጣ ያንን መልሶ ለማግኘት ሲል የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖር ይሆናልና አያስደንቀኝም፣ ግን ማስታወቂያውን በማቅረብ የሚተባበሩት ድረ ገጾችና በእሱ ዙርያ ተሰባስበው የሚያጨበጭቡት ፖለቲከኛ ተብዬዎች ከሰውየው የባሰ ያሳፍሩኛል።

ሌላው የዚህ ዓይነት አስመሳይ ጀግና ደግሞ ስዬ አብርሃ ነው። ስዬም ቢሆን ልክ እንደ ገብሩ፣ ኢትዮጵያን በወያኔ ምክር ቤት ቁጭ ብሎ አጨብጭቦ ያስቆረሰ ከመሆኑም ባሻገር፣ ከነወንድሙ በወያኔ አገዛዝ ውስጥ ቁልፍ ሚና ይዞ ስንት ጥፋት ሲያጠፉ የኖረ ሌላ ሃገር በታኝ ሲሆን፣ ሰሞኑን በየድረ ገጹ ኢትዮጵያን ሊያድን እንደመጣ መሲህ ተደርጎ፣ ዛሬ አሜሪካ ውስጥ፣ ነገ ደግሞ ካናዳ ላይ ንግግር ሊያደርግ ነው እየተባለ በየድረ ገጹና በየበራሪ ወረቀቱ እየቀረበ ነው። ወይ በየድረ ገጹ የሚያቀርቡት ሰዎች እየቀለዱበት ነው፣ ያለበለዚያ ግን ወያኔ ተቃዋሚዎቹን ለመበታተንና ለመከፋፈል በሽፋን የላከው የውስጥ አርበኛ መሆን አለበት። ያለበለዚያማ ስዬ ሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ለንግግሩ እንኳን ለከት የነበረው ግለሰብ አልነበረም።

አንዱ ኮሜዲያን ደግሞ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚባለው እስስት ነው። በአንድ ወቅት ኢሕአፓ፣ ቀጥሎ ወያኔ አሁን ደግሞ ቅንጅት ወይም የቅንጅት ግንጣይ ነኝ ብሎ፣ ሚዛን ወዳጋደለበት ሁሉ እያጋደለ፣ ዛሬ ያለውን ነገ እየሻረ፣ ዘንድሮ የደገፈውን ለከርሞ እየተቃወመ፣ አንድ ወጥ አቋም ሳይኖረው፣ በተገኘው ዘዴ ሁሉ ሥልጣን ላይ ለመውጣት የቋመጠ ግለሰብ ነው። ካልተሳሳትኩ፣ ይሄ ግለሰብ የወያኔ ባለሟል ሆኖ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ይሁን ምክትል ብቻ አንድ ሥልጣን ማዘጋጃ ቤት አካባቢ የነበረው ይመስለኛል። በአንድ ወቅት ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር ለመከፋፈል ሲነሳ፣ የወያኔን መፈክር አንግቦና ጌቶቹን ለማስደሰት ብሎ ስለ አማራው አንድ የማይረባ ጽሁፍ ጽፎ ነበር። ከዚያ ከጌቶቹ ሲጣላ፣ እንደገና ወያኔን አውግዞና በፊት የጻፈውን ጽሁፍ አስተባብሎ ለመቅረብ ሞከረ። አሁን

ደግሞ ከኔ ወዲያ ፖለቲከኛና ወያኔን ተቃዋሚ ለአሳር ነው ብሎ፤ ያቺ አንዴ ቀምሷት ገና በደንብ ሳያጣጥማት ከእጁ የወጣች ሥልጣን እያስቋመጠችው ነው መሰለኝ፤ ለሥልጣን እየተቅበዘበዘ ነው።

አንድ ሁሉም ላይ በጋራ የማየውና የማይገባኝ ነገር ግን፤ ሁሉም የወያኔ አባላትና አደግዳጊዎች የነበሩ ሲሆኑ፤ ስንቱን ንጹህ ሰው አግቶ ያለው ቂመኛ ወያኔ፤ እንዴት ነው እነሱን ተቃዋሚዎች መሆናቸውን እያወቀ፤ ከሃገር ቤት በቦሌ ሰተት ብለው እንዲወጡ ያደረጋቸው? የዚህን ያህል ተቃዋሚዎቹን የማይፈራና ይቅር ባይ ከሆነስ ለምንድነው በየጨለማ ዋሻው ያሰራቻውን ሌሎች ተቃዋሚዎቹን ያልፈታው? የሚሉ ጥያቄዎች ይመጡብኝና፤ እነዚህ ሰዎች ሌላ ተልዕኮ ያላቸው ይሆናሉ ብዬ አስባለሁ።

ብቻ እነዚህ ሰዎች፤ እንደሚያወሩት ሃገሪቱን *“ለማዳንም”* ሆነ ወይም ሌላ ተልዕኮ ኖሯቸው፤ ማለትም ተቃራኒውን ሊያዳክሙም ሆነ ሊበትኑ፤ ተመልሰው ፖለቲካ ውስጥ ገብተው የሚያቦኩት፤ በእኔ አስተያየት ቀደም ሲል ዕድል አግኝተው ዕርግጠኛውን ማንነታቸውን ለህዝብ ያሳወቁ በመሆናቸው፤ አሁን ተነስተው አንዴ *“ንስሃ ገብቻለሁ”* አንዴ *“ከስህተቴ ተምሬያለሁ”* በማለታቸው ብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሞኝቶ እንደመሪ ሊወስዳቸውና ተመልሰው ወደ ሥልጣን ኮርቻ የመውጣት ዕድል ሊሰጣቸው የሚገቡ አይደሉም። እነዚህ ሰዎች ልክ ከኳስ ሜዳ በቀይ ካርድ እንደተባረረ ተጫዋች መድረኩን ትተው ወጥተው የፖለቲካውን ትግል ለሌሎች መልቀቅ አለባቸው። በተለይም፤ ከደርግም ሆነ ከወያኔ ጋር ሲያቧችሩ ኖረው፤ የማይሽር ጠባሳ በታሪክ ላይ ጥለው ያለፉ የፖለቲካ ውርዴዎች፤ ከሕብረተሰቡ ፈንጠር ብለው ተቀምጠው የውርዴ ቁስላቸውን እያስታመሙና እየላሱ ተደብቀው ይቀመጡ እንጂ፤ በውርዴ እጃቸው የሃገራችንን ፖለቲካ ባይነካኩት ጥሩ ነው።

ከፈለጉ፤ ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት ዱሮም ቢሆን የቂጢኛም ውሎ ከውርዴ ነውና እነስዬ፤ ገብሩ፤ አንዳርጋቸውና  ሌላም ያልጠቃቀስኳቸው እንደነ ነገደና አረጋዊ የመሳሰሉ የፖለቲካ ውርዴዎች ተሰባስበው፤ *“ሁለት ፈሳሞች ሲገናኙ ሽታዬ ሽታዬ ይባባላሉ፤”* እንደሚባለው፤ ከዘመኑ ፖለቲካ ራሳቸውን አገልለው ሥልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን ስለፈጸሙት *“ጀግንነት”* እርስ በርሳቸው እየተሞጋገሱ ከመቀመጥ የሚከለክላቸው የለም። ግን በምንም ዓይነት የኢትዮጵያ ፖለቲካ *“የፖለቲካ ውርዴዎች”* መጫወቻና መቀለጃ መሆን የለበትም። እነዚህ ሰዎች እኮ አብዛኛዎቹ በወያኔ አንዳንዶቹ ደግሞ በደርግ ቂጢኝ የተለከፉና ድነናል ብለው የሚያስወሩ ውርዴዎች ናቸው!!

አንዳንድ ሰዎች *“አንድ ጊዜ ተጸጽተው ይቅርታ ጠይቀዋልና ለምን እንደዚህ እናመርርባቸዋለን?”* እያሉ ሁለተኛ ዙር ሃገር የማጥፋት ዘመቻቸውን እንዲቀጥሉ ዳግመኛ ዕድል ሊሰጧቸው ይፈልጋሉ። በይቅርታ የሚታለፉና ዳግመኛ ዕድል የሚያሰጡና፤ ጭራሽ ለአንድ ጊዜም እንኳን ቢሆን ይቅርታ የማያሰጡ ጥፋቶች አሉ። በመንገድ ላይ ሲጓዝ በስህተት እሰው እግር ላይ የቆመ መንገደኛ ይቅርታ ቢጠይቅ ሊሰጠው ይችላል፤ ይገባልም። ግን በአንድ የታሪክ ወቅት ሥልጣን ላይ

ተቀምጠው፤ ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀም ሆነ ብለው ሃገር ቁጭ ብለው አጨብጭበው ሲያስቆርሱ፤ አንዱን ሕዝብ በሌላው ላይ አነሳስተው ሲያጋድሉና ከፍተኛ የአስተዳደር በደል ሲፈጽሙ የነበሩ ሁሉ ተነስተው፤ *“በፊት ለገደልናቸው ሰዎች ይቅር በሉን፤ ግን ሌሎች ያልጨረስናቸው ሰዎች ሰላሉ ሌላ ዕድል ይሰጠን፤”* ዓይነት የብልጥ ጥያቄ ሲያነሱ ማስተናገድ፤ ሞኝነት ወይም ጅልነት ነው። ሞኝን እባብ ሁለት ጊዜ ነደፈው እንደሚባለው ሁለቴ መሞት ያለብን አይመስለኝም።

በተለይ ስዬ አብርሃኮ የአሁኑን፤ ማለትም ትንሽ እስር ቤት ውስጥ ከታሸ በኋላ፤ ጸባዩን አላውቅም እንጂ፤ በሥልጣን ላይ በነበረበት ዘመን ሳውቀው፤ በሚናገረው ነገር ላይ ሁሉ በግልጽ ዕብሪትና ድንቁርና (arrogance and ignorance) የተነባበሩበት ግለሰብ ነበር። አሁንም ደርሶ ሃገር ወዳድና ሥነ ሥርዓት ያለው ሰው መስሎ ለመታየት ቢሞክርም፤ እዚያ ሥልጣን ላይ ሲቆናጠጥ ዕውነተኛ እሱነቱ ተመልሶ ላለመምጣቱ ምን ማረጋገጫ አለ? ስለዚህ እሱን እዚያው በጠበል ብታርቁልን እንወዳለን። በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ያሳይ የነበረውን ባሕሪዩን ገና ሳንረሳ *“ኢትዮጵያን የሚያድን፤ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ”* እያላችሁ ባታሞካሹት ጥሩ ነው። በዕርግጥ በሃገሪቱ ላይ ያንዣበበው ወያኔ የጠነሰሰልን ሴራ እጅግ በጣም የከፋና ሃገሪቱንም ወደጥፋት እያመራ መሆኑን ብናውቅም፤ ወላድ በድባብ ትሂድ እንጂ፤ ኢትዮጵያ ብዙ አርቆ አሳቢ፤ ለሕዝብ ፍቅርና አክብሮት ያላቸው፤ ሃገራቸውን ከራሳቸው የሚያስቀድሙና አንገታቸውን ደፍተው የተቀመጡ፤ እንደነ ገብሩና ስዬ በመንደር የተወሰነ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ራዕይ ያላቸው ልጆች አሏትና፤ የፖለቲካ ውርዴዎችን አትሻም።

ድረ ገጾችም ብትሆኑ፤ ገና ለገና ገንዘብ እናገኛለን ብላችሁ የፖለቲካ ውርዴዎችን የጀመሩትን ጥፋት እንዲጨርሱ ወደ መድረክ እየጋበዛችሁ የቀረችዋን ሃገራችንን አትበታትኗት። ድረ ገጻችሁን ለሃገር የሚበጅ ነገር ማቅረቢያ እንጂ፤ ***“የፖለቲካ ውርዴዎች”*** መፈንጪያና መነገጃ አታድርጉት።

----////----

* በነገራችን ላይ *“የፖለቲካ ውርዴ”* የምትለዋን ቃል በመዝገበ ቃላት ውስጥ ብታስገቡልኝና ባለቤቷም እኔ መሆኔን ብትመዘግቡልኝ ደስ ይለኛል።